# ምሁር ማነው ምን ይጠበቅበታል?

ምሁራን በምሁርነታቸው መጫወት ስለሚገባቸው ሚና ከዚህ በፊት ብዙ ሔንደተባለና እንደተጻፈ ይታወቃል፣ሆኖም ዐውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንደሚባለው እውነተኛ ምሁራን፡ካካበቱት የጠለቀ ዕውቀትና የዳበረ፡ልምድ በመነሳት የሚሰጡትን ትምህርትና ጠቃሚ ምክር ወደ ጎን በመተው በተለያዩ ምክንያቶች ለተለያዩ ዓላማዎች ከቆሙ ወገኖች ጎን በመሰለፍ የግል ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሩዋሩዋጡ ከእውነትና ከሕዝብ ጋር እየተጋጩ የሁዋላ ሁዋላ የስነልቦና ተጠቂ በመሆን፣በሞራል ውድቀት ጭምር የሚሰቃዩ፣በምሁርነታቸው ሁኔታዎችን ገምግመው የወደፊት ዕይታ የሌላቸው ጥቂቶች እንዳልሆኑ በየጊዜው የሚታይ እውነታ ነው።

ምሁር የሚለውን ቃል በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ዲግሪ የጨበጠውና ወደ ህብረተሰቡ መሃል ሲገባ ግራ በመጋባት ያልሆነውንና ሊሆን የማይችለውን መሆን የሚከጅለው ሁሉ ምሁር ካልተባለ በስተቀር፣የተማረ የተመራመረ የሚለው አባባል ሊገልጸው ይችላል ብዬ አምናለሁ።በሌላ አገላለፅ በትምህርት ዓለም ቆይታቸው የቀሰሙትን ዕውቀት በበለጠ ጥናትና በምርምር ሥራ በማጎልበትና በማዳበር ውጤታማ ሥራ እየሰሩ በሙያቸውና፡በስነ-ምግባራቸው፣እንዲሁም ለሰው ልጅ ሙብት መከበር በምሁርነታቸው ማበርከት የሚገባቸውን እያበረከቱ የሕዝብ ከበሬታ ያገኙትን ለማለት ፈልጌ ነው።

በእርግጥ የተማረና የተመራመረ ሰው ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባው ለእውነት፣ለፍትህ፣ለትክክለኛ ሥራ፣በአጠቃላይ ለሀገር ጠቃሚ ለሆኑ ነገሮች፣ እንዲሁም ዘርና ሃይማኖት ሳይለይ ለሰው ልጆች ሙብት መከበር መሆን ነበረበት።ታዲያ የተማረ ሁሉ ለነዚህ የሕዝብን ትኩረት ለሚስቡ ቁም ነገሮች ቅድሚያ ይሰጣል ብሎ በጅምላ መናገር ይከብዳል፣ምክንያቱም በተለያዩ አስነዋሪ ፀብዮችና የዘመኑ ህክምና ሊያድናቸው በማይችል በሽታዎች እየተለከፉ ከትምህርት ደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ሥራ በመሥራት ከበሬታቸውን እየቀነሱ፣በትዝብት ዐምድ የሰፈሩ ምሁር ነን ባዮች እንዳሉ አያከራክርምና ነው።

ለምሳሌ የህል-መለማመጥ ሌላው የመንጠቂያ መሣሪያ ነው እንደሚባለው በዚህ አደገኛና ጎጂ መሣሪያ እየተጠቀሙ ጎጂ ሥራ የሚሠሩ፣በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታዋን የተማመነች... እንደሚባለው ጊዜና ሁኔታ ተመቻቸልን ብለው አለኛ ዐዋቂ ላሳር በሚል ልክፍት ተለክፈው፣እራሳቸውን ከሚገባው በላይ በመካብ ከሙያቸው ውጪም የፈለጉትን እንደፈለጉ እየሰሩ አካኪ ዘራፍ የሚሉና ለጥቃቅን ጥቅሞች ንፁሃንን መስዋዕትነት ሲያቀርቡ ህሊናቸውን የማይቆረቁረው፣ባጠቃላይ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ሲደረግ እያዩ የህሊና ፀፀት እንኩዋን የማይሰማቸው በምሁር ካባ የተሸፈኑ ጥቂቶች አይደሉም።

በፖለቲካው መስክም ወዲያ ወዲህ በመሩዋሩዋጥ ሥልጣን ከጨበጡ በሁዋላ እውነትንና ዲሞክራሲን ሳይሆን፣መጠቀሚያ ወንበራቸውን ለማስከበር የተለያዩ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ፣የሚናገሩትና የሚሠሩት ባለመጣጣሙ ውጤት አልባ የሆኑ፣ከስህተታቸው በመማር የማይታረሙ የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት ሲሉ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተሻለና ጥሩ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉበትን ሙያቸውን ትተው በአታላይ ፖለቲከኞች ነን ባዮች እንደ አሽከር የሚገዙ አሉ። ጊዜ የሰጠው ወገን መሳሪያ ሆነው እንዲሠሩ

የሚመደቡ "የምሁር"ፖለቲከኞች ሁሉ ሕዝባዊ ወገንነታቸው እየኮሰሰ ኢ-ዲሞክራሲ ሥራቸው እየጎላ ይታያል።

ከሕዝብ አብራክ እንዳልወጡና በሕዝብ ሀብት እንዳልተማሩ ሕዝብ የሚጠላውን መንግሥትና ሥርዐት ለማጎልበት ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩና በአሁኑ ጊዜም ካለፈው ስህተት ባለመማር ተመሳሳይ ስህተት የሚሠሩ „ምሁራን" ነን ባዮች ስለመኖራቸው ማውጋቱ ለቀባሪ ማርዳት ስለሚሆን ማለፉ ይመረጣል።በእኔ እምነት ከአንድ ምሁር የሚጠበቀው ትልቅ ቁምነገር እንደ ጥሩ መምህር የተማረውንና የሚያውቀውን ዕውቀት እውነታውን ሳያዛባ ማቅረብና ፍርድና ውሳኔውን ለጠተቃሚው አካል መተው እንጂ የኔን አቋዋም ካልተከተላችሁ፣እኔ የምለውን እንዳለ ካላስተጋባችሁና በተግባር ካልገለፃችሁ የሚል ከሆነ ፍፁምነት የለምና ስህተት ነው ባይ ነኝ።

በእርግጥ በጅምላ መኮነን ማለትም መተቸትም ሆነ በጅምላ ማመስገን ተገቢ ባለመሆኑ ሻማ እራሱ እየተቃጠለ ለሌላው ብርሃን ይሠጣል እንዲሉ፣ ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም ሲሉ ዐቅማቸው፣ችሎታና ሁኔታ እንደፈቀደ ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል ትክክለኛ የምሁርነት ተልኮአቸውን ለተወጡና በመወጣት ላይ ላሉ እውነተኛ ምሁራን ያለኝን ከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት በዚህ አጋጣሚ እየገለፅኩ፣በግርድፉ ቁዋንቁዋዬ የገለፅኩዋቸውን፣ ጎጂ የምሁር ነን ባዮች ፀባይና ተግባር እንዴት መዋጋትና ማስቀረት እንደሚቻል፣ በተጨማሪም ምሁር የሚለውን ቃል ለመጠቀም የሚያስችሉ መመዘኛ መስፈርቶችን ሊያሳውቁን የሚችሉ ወገኖች ቢተባበሩ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። ይህን ጥንቅር ከዚህ በፊት ለጠቢያ መጽሔትና ጋዜጣ አዘጋጆች ልኬ በእንነጋገር ዐምዳቸው ላይ አውጥተውት እንደነበር በዚህ አጋጣሚ ለማሳወቅ እፈልጋለሁ።

ሐዲስ ለማ።<br>
ከጀርመን።<br>
ሰኔ 2001<br>
June 2009